የአቶ ነጋ ወዳጆ ቱራ

አጭር የህይወት ታሪክ 7/12/1953-01/31/2018

አቶ ነጋ ወዳጆ ከአባታቸዉ ከአቶ ወዳጆ ቱራ እና ከእናታቸዉ ከወይዘሮ ቢጂግዱ ጃዊ በቀድሞ ስሙ ኢሉባቦር ክፍለ አገር ከበደሌ ከተማ ወጣ ብሎ ስዲሳ በመባል በሚታወቅ አካባቢ ልዩ ስሙ ጫንጮ በተባለ መንደር ዉስጥ በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ሃምሌ 3 ቀን 1945 ዓ.ም ተወለዱ።

አቶ ነጋ ወዳጆ ዕድሜያቸዉ ለትምህርት ሲደርስ በዚያዉ በአቅራቢያዉ በሚገኝ የህዝብ ትምህርት ቤት ለረጅሙ የትምህርት ጉዞ መዘጋጃ የሚሆናቸዉን ትምህርታቸዉን ጀመሩ።የአንደኛና የመለስተኛ ደረጃ ትምህርታቸዉንም በበደሌና ቀጥሎም በጎሬ በሚገኝ ከፍተኛ ደረጃ ት/ቤት አስቸጋሪዉንና እልህ አስጨራሱን የመጓጓዣና የስንቅ አቅርቦት ፈተና በመጋፈጥ ትምህርታቸዉን እጅግ አጥጋቢ በሆነ ዉጤት አጠናቀዋል።

አቶ ነጋ ወዳጆ ምንም እንኳን የመጀመሪያ ግደታቸዉና ሀላፊነታቸዉ የወላጆቻቸዉን የዕለት ተዕለት የኑሮ ዉጣ ዉረድ ማገዝ መሆኑን ቢገነዘቡም የትምህርትን ጠቀሜታና ለራሳቸዉም ሆነ በቅርባቸዉ ላሉ ቤተሰቦቻቸዉና ለሀገራቸዉም የሚያስገኘዉን ፋይዳ ገና ከጠዋቱ የተገነዘቡ በመሆናቸዉ በመንገድ ላይ ያጋጠሟቸዉን ፈተናዎች በመቋቋም ይህንን ጽኑ ዓላማቸዉን ለማሳካት በደብረ ብርሃን የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ የሁለት ዓመት ስልጠና ተከታትለዉ በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በ1964 ዓ.ም በመመረቅ ባስመዘገቡት አጥጋቢ ዉጤት በዚያዉ በማሰልጠኛዉ በመምህርነት በመመደብ የመጀመሪያ ስራቸዉን በ19 ዓመት አፍላ ዕድሜያቸዉ ጀመሩ።

አቶ ነጋ ወዳጆ በደብረ ብርሃን የመምህራን ማሰልጠኛ ቆይታቸዉ በስራ ባልደረቦቻቸዉ፡ በተማሪዎቻቸዉና በህብረተሰቡ ዘንድ እጅግ የተከበረና ተወዳጅ ምግባረ ሰናይ ያላቸዉ በመሆቸዉ የልጅ ስማግሌ በሚል ይታወቁ እንደነበር የረጅም ጊዜ ጓደኞቻቸዉ ምስክሮች ናቸዉ።

አቶ ነጋ ወዳጆ ከትምህርት ማዕድ የሚገኘዉን የዕዉቀት ጥማታቸዉን ለማርካት ከነበራቸዉ ጽኑ ፍላጎት የተነሳ በአዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ በኢኮኖሚክስ የትምህርት መስክ ትምህርታቸዉን በመከታተል በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1980 ዓ.ም በመጀመሪያ ድግሪ በከፍተኛ ዉጤት ተመርቀዋል። ቀጥሎም በኢትዮጵያ ሜትዮሮሎጂ አገልግሎት በፕላንና ፕሮግራም መምሪያ ከጀማሪ ኤክስፐርትነት እስከ መምሪያ ሃላፊነት ደረጃ በተለመደዉ ጥልቅ የሀገር ፍቅር ስሜትና ተቆርቋሪነት ለ 7 ዓመታት ወገናቸዉንና ሀገራቸዉን አገልግለዋል።

አቶ ነጋ ወዳጆ ባገኙት የዉጭ አገር የትምህርት ዕድል እጅግ ከሚወዱትና ከሚሳሱለት ወገናቸዉና ሀገራቸዉ ተለይተዉ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርታቸዉን ለመከታተል በማሰብ በአሜሪካን ሀገር ኑሮአቸዉን ላለፉት 24 ዓመታት ቤተሰባቸዉንና ወገቸዉን ሊጠቅሙ በሚችሉ የስራ ዘርፎችና ሀላፊነቶች በመሰማራት እስከ የህይወት ፍጻሜያቸዉ ጥቂት ቀናት ድረስ የዘወትር መገለጫቸዉ በሆነዉ በማይናወጽ ፅናት ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል።

አቶ ነጋ ወዳጆ ከወይዘሮ ስርጉት ደምሴ ጋር በመስከረም ወር 1997 ዓ.ም ከመሰረቱት ትዳር እንደ ዓይናቸዉ ብሌን የሚሳሱለትንና በፍቅርና በጥሩ ስነ ምግባር እንድያድግላቸዉ የሚመኙት የ12 ዓመት ወንድ ልጅ አባት ነበሩ።

አቶ ነጋ ወዳጆ ቋሚ ኑሮአቸዉን በሜሪላንድ ከመሰረቱ ጀምሮ በአካባቢያቸዉ ህብረተሰብ እጅግ የተከበሩ ስርዓት አክባሪና ላመኑበት ዓላማና ለእዉነት ሁሌም ግንባራቸውን የማያጥፉ ጠንካራ የቤተሰብ ሃላፊ እንደነበሩ ሁሉም የሚስማማበት ሀቅ ነዉ።

አቶ ነጋ ወዳጆ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባጋጠማቸዉ የጤና ችግር በህክምና ሲረዱ ቆይተዉ ባልተጠበቀ ሁኔታ በኢትዮጵያ አቆጣጠር ጥር 23 ቀን 2010 ዓ.ም በተወለዱ በ64 ዓመታቸዉ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

ልዩ ምስጋና

በዚህ ከፍተኛ የሃዘን ጊዜ ከጎናችን በመሆን ምን ጊዜም የማይረሳ ድጋፍ ላደረጋችሁልንና በዘወትር ጸሎታችሁ ለረዳችሁን ሁሉ ምስጋናችንን ከልብ እናቀርባለን። ባለቤታቸዉ ስርጉት ደምሴ ልጃቸዉ ጊዲዮን ነጋ